

# ፅናት

*ሥርጉተ ሥላሴ*

አውራ! ወጋግራ! ዓምደ ብራ የሚያበራ የሚገራ ፍርሃትን ስጋትን ጭንቀትን የሚመክት። የውስጥ ደም ፈተናን የመቋቋም አቅምን፤ ብቃትን፤ ልኬታን የሚበይን ክቡር ሥነ ምግባር ነው። አጥንትን ሰርስሮ የሚፈትሽ። እራስን በእራስ የሚዳኝ።

መብላትም መጠጣትም፤ ድሎትም መከፋትም፤ መኖርም ማለፍም ሁሉም በጊዜያቸው መዋዕለ ዕደሜያቸውን ተክዘው ይበናሉ ይተናሉ። የሕይወት ዥንጉርጉር ገጠመኝም እንደ ዕጣ ፋንታው ሊመንን ወይ ሊመነኩስ ወይም ዓለምን መስሎ ሊያድር ይችላል።

ሀገራዊ ብቃትን የሚመዝኑ ችግር እና መከራን ተቋቁሞ ለሚያልፍ ዕድሜ፤ ለዕልፍ የደም ዕንባ ዕልፍ ብሎ ሃሳርን በፀጋ እና በሃሴት መቀበል፡ አልፎ ተርፎም ሞትን ቅደመኝ ብሎ በቃል መፅናት ግን የሰንደቆቹ ሁሉ ጉልላት ነው።

ቃል ቃል ነው። ቃል ቃልነቱ ቃል ሆኖ ፋና የሚሆነው ግን ቃል አሳላፊው ለቃል ኪዳኑ ሲያደገድግ፣ ሲሰግድ ቃሉን ለቃሉ በተግባር ሲያሰጌጥ ብቻ ይሆናል።

ይህ ደግሞ የሁለመናን ከብረት የተሰራ ፅናትን ይጠይቃል። ወጀብ፤ ዓውሎ፤ ጎርፍ ሳያሸንፈው፡ እንደ እንስሳ ለከርስ ሳያድሩ መፋለምን፤ መቁረጥን፤ መወሰንን ይጠይቃል። ግለኝነትን ድል ነስቶ ለሚሊዮን ብሶት ዘብ መቆምን ይጠይቃል እራስን ይፈትናል ያፋጥጣል።

*

<u>ፅናት</u> ታማኝነትን አፍልቆ መሆን መቻልን ይገብራል። ግልብ ሰራሽን ውስጥነት አንጠሮ ምልከት ዓርማ ይሆናል። የሴልን የነርቭን የጅማትን ህዋስ እንደ ወርቅ ያነጥራል። የመስዋትነት ቃና ዘጉባኤ ይሆናል።

ፅናት ማንነትን አጉልቶ እራስነትነ ይተርጉማል። ከዘመናችን ብርቱ፤ ጠንካራ፤ ታታሪ መሪዎች አንዷ ብርቋ ከሆኑት ከጀግናዋ ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ ያገኘነው ዘመን የማይሽረው፤ ወቅታት የማያ-ወይቡት፤ ጊዜ የማያፋድስው የሀቅ እንክብል ይህ ነው።

ስለሆነም ትውልድ ለማይተካቸው ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር በተግባር ያጌጠ መከራን በፍቅር ተቀብሎ ላሰተናገደ ጀግንነታቸው አቻ የለሽ ፅናታቸው ..... የመታገያ የጋራ ዓርማችን ነው።

ጀግንነት ፋሽስትን ድል ነሰቶ ህዝባዊ ፍቅርን በምፅላት በእያንዳንዳችን ህሊና ሲከትም በእድሜዬ ያዬሁት በክብርትነታቸው ነው። ስለሆነም „ውረሰ ጽናትን“ በልቦናዬ አብቅሎ ያለማ ዘንድ መዳኀኔዓለም አባቴን ተንበርክኬ በአፅህኖት እለምነዋለሁ።

ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር  የቃል አርበኛ፤ የቃል አብዮተኛ፤ የቃል ሁነኛ፤ የቃል አሥራት፤ የጽናት ጉልላት የተናገሩትን ሆነው የተገኙ የእኩልነታችን  ሰንደቅ ፋና ወጊ ናቸው።

በውስጤ ያለው የፅናት ራዕይ በክብርትነታቸው ዙሪያ ቋሚ የሆኑ ተግባራትን ያካትታል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በሲዊዘርላንድ በዙሪክ ከተማ ራዲዮ ፕሮግራም መጀመር ነው። በሌላ በኩል በድኅረ ገፁም የተገባውን ያህል አትኩሮት መስጠት።
…

ካለ ሴቶች ንቁ እና ብርቱ ተሳትፎ የፀረ ወያኔ ትግሉ ዓላማ እግቡ አይደርስም!
ወርቅን ያነጠረ ፅናት የዕድሜ ልክ ዕንቁ ነው!
ነፃነት በወያኔ እስር ለሚማቅቁት  ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር እና በወያኔ እስር ለሚማቅቁ ወገኖቻችን ሁሉ!
ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!